# የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ

ትምህርት ሚኒቴር
ታህሳስ 2005
አዲስ አበባ

**ማውጫ**

| ይዘት | ገጽ |
|---|---|
| 1. ዳራና አስፈላጊነት | 1 |
| 2. የሙያዊ ብቃት ስታንዳርዱ ትኩረት | 2 |
| 3. የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ አደረጃጀት | 4 |
| 3.1 ለትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች የሚያስፈልጉ ሙያዊ ርዕስ ጉዳዮች | 4 |
| 3.1.1 ራዕይና እሴቶች | 5 |
| 3.1.2 የግለዊ በህርይ ዓይነቶችና ማህበራዊና የግንኙነት ክህሎቶች | 5 |
| 3.1.3 እውቀትና ግንዛቤ | 5 |
| 3.1.4 የሙያዊ ተግባራት ክንውን | 6 |
| 3.2 የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶች | 6 |
| 3.2.1 ስታንዳርድ 1፦ በሙያዊ የተግባራት ክንውን ሂደት ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለኑሮ በመማር ለሕይወት ሙሉ ትምህርት አርአያ ሆኖ ማነቃቃት፣ | 6 |
| 3.2.2 ስታንዳርድ 2፦ ለትምህርታዊ ጥናትና ምርምር ትምህርት ቤቶችን ማነሳሳት፣ ማካሄድና መምራት | 7 |
| 3.2.3 ስታንዳርድ 3፦ በትምህርታዊ ተግባራት ክንውኖች ሂደት ወቅታዊ እውቀትንና ግንዛቤን ሥራ ላይ ማዋል። | 8 |
| 3.2.4 ስታንዳርድ 4፦ ውጤታማና አሳታፊ የትምህርት ቤት አመራርና አስተዳደርን መተግበር | 9 |
| 3.2.5 ስታንዳርድ 5፦ በምህርት ቤቶች ሊሟሉ የሚገቡ አስፈላጊ ሁኔታዎችን መለየትና መተርጎም | 10 |
| 3.2.6 ስታንዳርድ 6፦ ራስን፣ ግለሰብንና ቡድንን መገንባት | 10 |
| 3.3 የክንውን አመላካቾች | 11 |
| 3.4 አራቱ የሱፐርቫይዘሮች የሙያዊ እድገት ደረጃዎችና ችሎታዎች | 11 |
| 3.4.1 ጀማሪ ሱፐርቫይዘሮች | 11 |
| 3.4.2 ብቁ 1 ሱፐርቫይዘሮች | 12 |
| 3.4.3 ብቁ 2 ሱፐርቫይዘሮች | 12 |
| 3.4.4 መሪ ሱፐርቫይዘሮች | 13 |

**14**

## አባሪዎች


| | |
|---|---|
| **አባሪ 1፦ የሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶች ጥቅል ቻርት** | 14 |
| **አባሪ 2፦ የሱፐርቫይዘሮች መሠረታዊ ስታንዳርዶች፣ ንዑሳን ስታንዳርዶችና የክንውን አመላካቾች** | 15 |
| **አባሪ 3፦ ከአራቱ የሱፐርቫይዘሮች የሙያዊ እድገት ደረጃዎች ጋር የተቀናጁ የሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶች** | 23 |
| **አባሪ 4፦ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶች ማረጋገጫ መምሪያ (Evidence Guide)** | 32 |
| **አባሪ 5፦ የቁልፍ ቃላትና ሐረጎች ትርጉም፦** | 34 |

# የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ

## 1. ዳራና አስፈላጊነት

የትምህርት ተደራሽነትን፣ ጥራትን፣ ፍትሐዊነትን፣ ውጤታማነትንና ተገቢነትን ማረጋገጥ በትምህርት ሥርዓቱ በሁሉም ደረጃ ውጤታማ አመራርና አሠራር እንደሚጠይቅ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው አስቀምጧል። ይህን የፖሊሲውን መሠረታዊ ነጥብ በማስፋት የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅም የትምህርት ቤት መምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች አቅም ግንባታ ስልትን የትምህርት ቤቶችን መሻሻል ከማመቻቸትና ከመደገፍ ግልጽ ዓላማ ጋር አካቶ ይዟል። የአገሪቷ መምህራን ልማት መርሀግብር አፈጻጸም ገዥ መመሪያም እንደ አጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ አካል ለትምህርት ቤቶች መሻሻል ራዕይና ስትራቴጂያዊ እቅድ ዝግጅትን ጨምሮ ከተለያዩ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች አኳያ ለትምህርት ቤቶች ውጤታማ ድጋፍ ሊሰጡ ለሚችሉ የትምህርት ቤት አመራሮችና ሱፐርቫይዘሮች አስፈላጊነት ትኩረት ሰጥቷል።

ለመምህራንና ትምህርት ቤት አመራሮች ልማትና ብቃት ማረጋገጫ የግልጽና ውጤታማ ሥርዓት መኖር ለተማሪዎች የሚሰጠውን ትምህርት ጥራት መረጋገጥ የማይታለፍ ቅድመ ሁኔታ መሆኑ በአራቱም የትምህርት ሰክተር ልማት ፕሮግራሞች ተጠቅሷል። በዚህ መሠረት በፖሊሲውና በአራቱ የትምህርት ሰክተር ልማት ፕሮግራሞች ትግበራ ሂደት አገሪቷ በትምህርቱ ሥርዓት ጠቃሚ መሻሻሎችን (እድገቶችን) አሳይታለች። የግብዓቶች የእድገት መስመርን ተከትሎ የትምህርት ተደራሽነት በሥርዓቱ በሁሉም ደረጃ ፈጣን እድገትን አሳይቷል። ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ቡድኖች ታዳጊ ክልሎችን ጨምሮ በሁኔታዎች መሻሻል ልዩነቶች ግምት ውስጥ በሚገባ ደረጃ ቀንሰዋል።.

ይሁን እንጂ በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ከጥራት አኳያ መፍትሔ ያላገኙ ተግዳሮቶች አሁንም እንዳሉ የወቅቱ እንቅስቃሴ እያሳየ ነው። ይህ ደግሞ ከተማሪዎች ውጤት ማሽቆልቆል አኳያ ብቻ ሳይሆን ከመምህራንና ከትምህርት ተቋማት አመራሮች ተግባራት ክንውን ጥራት መቀነስም እንደሆነ ታውቋል። ከሁለተኛው ቁልፍ ግብዓት ማለትም ከትምህርት ቤት አመራርና አስተዳር አኳያ ያለው ድክመት የሚገለጸው በትምህርት ሥርዓቱ በደካማ ሱፐርቪዥን (ድጋፍና ግምገማ)፣ አመራርና አስተዳደር ሂደት ሲሆን በተራው በመማሪያ ክፍሎች የሚሰጠው ትምህርት ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ ይገኛል።

ከዚህም የተነሳ በ3ኛው የትምህርት ሰክተር ልማት ፕሮግራም ቅድሚያ ተሰጥቶት የነበረው የትምህርት ቤት አመራር ሙያዊ ጥራት የመጠበቅና የመቆጣጠር ሥራ ከመምህራን ሙያዊ ጥራትና ልማት ጥበቃና ቁጥጥር ጋር ተጣምሮ በ4ኛው የትምህርት ሰክተር ልማት

ፕሮግራምም ቅድሚያ ከተሰጣቸው ትላልቅ ተግባራት አንዱ ሆኖ ቀጥሏል። የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራር ሙያዊ ልማት ጥራትን ለመጠበቅና ለመቆጣጠር በብዙ ጥቅም ላይ ከዋሉ ስትራቴጂዎች አንዱ የሙያዊ ብቃት ደረጃዎችን (ስታንዳርዶችን) በማዘጋጀት መተግበር ነው። ስለዚህ የዚህ ሰነድ ጥቅል ዓላማ ለሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ደረጃ መወሰን ነው። ለሱፐርቫይዘሮች  የሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ የማዘጋጀቱ መሠረት ሃሳብ በመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ስታንዳርድን መሠረት ባደረገ ሁኔታ ሊያልፉባቸው የሚገባቸው የሙያዊ እድገት ሥርዓት መፍጠር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ስታንዳርዱን መረዳትና መተግበር የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች በስታንዳርዱ መሠረት የሚጠበቅባቸውን ሙያዊ ብቃት ማሟላታቸውን በምዘና በማረጋገጥ የሙያ ፈቃድ እንዲያገኙ ማስቻል ነው።

የስታንዳርድ ዝግጅት ጠቀሜታ በአብዛኛው መሠረት የሌለው የትምህርት ቤት ሱፐርቫዘሮች ምልመላን፣ ሥልጠናን፣ ምረቃን፣ ቅጥርንና ምደባን መከላከል ነው። አሁን እየታየ ያለውን ከትምህር ቤት ሱፐርቫይዘሮች ያለምንም የትምህርትና ሥልጠና ድጋፍ በሙያዊ የድጋፍ አሰጣጥ ክንውናቸው ውጤታማነትንና ስኬታማነትን እንዲያሳዩ የመጠበቅ ሁኔታን ለማስወገድም አስተወጽኦ ያደረጋል። ከሁሉም በላይ ግን የስታንዳርድ አቀራረብ የታለመው ቁልፍ የሙያዊ ብቃት ክፍተቶችን በምዘና ለመለየትና የተለየውን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን በመቀየስ ሱፐርቫይዘሮቹ ክፍተቶቻቸውን በመሙላት ብቁ ሆነው በሙያቸው እንዲቆዩ ለመገዝ ነው። በእርግጥም የሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድን በአራቱም የሙያዊ ብቃት ደረጃዎች ከሱፐርቫይዘሮቹ ሚናና ሃላፊነት ጋር አያይዞ ማየቱ የማይታለፍ ተግባር ነው።

እንደሚታወቀው በትምህርት ቤቶች ወጥ የአሠራር ሥርዓትን ለመፍጠር የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች መቆጣጠርን (የፖሊሲ፣ የስትራቴጂዎች፣ የደንቦችና መመሪያዎች ትግበራን በመከታተል ግብረ መልሶችን ከመስጠት አንጻር)፣ መደገፍን፣ መገምገምንና ተግባቦት መፍጠርን ጨምሮ ሦስት ስብስብ ተግባራትን ማከናወን ይጠበቅባቸዋል። የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች የላይና የታች እንዲሁም የጎንዮሽ ተግባቦቶችን ለማመቻቸት መቻል አለባቸው። ትምህርት ቤቶችን ከፖሊሲና ደንቦች እንዲሁም ፖሊሲ አውጪዎችን ከትምህርት ቤት ተጨባጭ ሁኔታዎችና ፍላጎቶች ጋር በማስተዋወቅ የላይና የታቹን ተግባቦት፤ በትምህርት ቤቶች መካከል የግንኙነት መረቦችን በመዘርጋትና መስተጋብሮችን በማመቻቸት የጎንዮሽ ተግባቦቶችን ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል። ይሁን እንጂ የእነዚህ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ተግባራት ተጨባጭነት ለሱፐርቫይዘሮች መሠረታዊ የሙያ ብቃት ስታንዳርድ በማዘጋጀት በትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ጥራት የማረጋገጥ ሥራ እንደ ዋና አካል መተግበርን ይጠይቃል።

ስለዚህ ይህ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች መሠረታዊ የሙያ ብቃት ስታንዳርድ የተፈለጉ ሙያዊ ብቃቶችን በማሟላት ከሚገኙ አራት የሙያዊ እድገት ደረጃዎች ጋር ተያያዥነት ባለው ሁኔታ ተዘጋጅቷል።

## 2. የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ ትኩረት

በእርግጥ በአገሪቷ በሁሉም ደረጃ (በፌዴራል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃዎች) በየሃላፊነት ድርሻቸው ሥር የተለያዩ ስያሜን ይዘው በትምህርት ቤት የትምህርት አሰጣጥን የሚከታተሉ ሱፐርቫይዘሮች አሉ። ይሁን እንጂ ይህ የሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ የተዘጋጀው በትምህርት ቤቶችና በክላስተር ትምህርት ቤቶች ዙሪያ ሙያዊ ክትትልና ድጋፍ እንዲሰጡ በወረዳ/ዞን/ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች ለተደራጁ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ብቻ ነው። እነዚህ የክትትል፣ የድጋፍና ግምገማ ሚና የሚጫወቱ፣ በትምህርት ሥርዓቱ ትምህርት ቤቶችንና የፖሊሲ አውጪዎችን ጨምሮ ከሌሎች የአመራር አካላት ጋር እንደዚሁም እርስ በእርስ እንዲገናኙ በማድረግ የላይና የታቹን እንደዚሁም የጎንዮሽ ተግባቦቶችን የሚያመቻቹ እንጂ የመስመር አስተዳደር አካል አይደሉም። ለትምህርት ቤቶች የታሰበውን መሻሻል ለማምጣት በትምህርት ቤቶች መካከል ተግባቦትን፣ የተሞክሮዎችና የልምድ ልውውጦችን ለማመቻቸት የጎንዮሽ ግንኙነቶችን የሚፈጥሩ ናቸው። በአጠቃላይ ስታንዳርዱ ለሚከተሉት የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ዋና ዋና የሃላፊነትና የተጠያቂነት ገጽታዎች ትኩረት ሰጥቷል።

### ሀ) ተማሪዎች ስኬታማ ዜጋ እንዲሆኑ ለትምህርታቸው ዋጋ በመስጠት እንዲማሩ በቁርጠኝነት መሥራት

የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች በትምህርት ቤቶች ለሚሰጡ ትምህርቶች በትምህርት ቤቶቹና በአካባቢው ማህበረሰቦች የጋራ ሊሆን የሚችል ከፍተኛ ደረጃ ያለው ራዕይ በመፍጠር ግልጽ የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው። የራሳቸውን ልምዶች፣ እምነቶችና ግምቶች ለመመርመር ፈቃደኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል። የጥናትና ምርምሮች ውጤቶችን በመገንዘብ ተግባር ላይ ማዋል፣ የሁሉም ትምህርት ቤቶች ማህበረሰቦች አባላት ተከታታይነት ባለው ሁኔታ መሻሻልን መደገፍና በዚህም የጋራ የሆነውን ራዕይ ትግበራን ለማረጋገጥ ራሳቸው ለከፍተኛ ተግባራት ክንውን ቁርጠኛ መሆን አለባቸው።.

### ለ) የመማር ማስተማር ሂደትን የትምህርት ቤቶች ተግባራት ማዕከል አድርጎ ማስቀመጥ፣

የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ እድገትን ወይም ልማትን፣ ምዘናን፣ ትምህርታዊ ስትራተጂዎችንና ሥርዓተ ትምህርትን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ጥናትና ምርምርን፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን፣ ተገቢ መረጃዎችንና ሌሎች ተጨባጭ መረጃዎችን መሠረት ያደረጉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ሃላፊነት አለባቸው። የተማሪዎች ውጤትን የሚያሻሽል ትርጉም ያለውና ውጤታማ ተሞክሮዎችን ለመውሰድ ምልከታዎችና ትብብሮች ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። የሁሉም ተማሪዎች ክብርና ስኬትን የሚደግፍ የትምህርት ቤት ባህልን ለመፍጠር የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ለልዩነቶች ትኩረት መስጠት አለባቸው። ለተማሪዎች መማር መሰናክሎችን በመለየት፣ ግልጽ በማድረግና በመያዝ ለተለያዩ ተማሪዎች የመማር ስትራቴጂዎችን የማዘጋጀት ጠቀሜታን ግልጽ ማድረግ

መቻል አለባቸው። ራሳቸው አርአያ በመሆን የእድሜ ልክ ትምህርትን የሚያበረታቱ ተማሪዎች መሆን አለባቸው። በተጨማሪም ለራሳቸውና ለትምህርት ቤቶች ማህበረሰብ አባላት ከፍተኛ ግምት የመያዝ ባህል መምሥረት ይጠበቅባቸዋል።

### ሐ) የትምህርት ቤቶችና የማህበረሰቡ ትብብር ለትምህርት ቤቶች አመራርና ተማሪዎች ስኬት ጠቃሚ ነው የሚለውን እውነት መረዳት

የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ትምህርት ቤቶችን እንደ የሰፊው ማህበረሰብ መሠረታዊ አካል በማየት ለውጤታማ ትምህርት ከሰፊው ማህበረሰብና ቤተሰቦች ጋር በቅንጅት መሥራትና መግባባትን መደገፍ አለባቸው። እየመጡ ያሉትን ጉዳዮችና የለውጥ ዝንባሌዎችን የመፈተሽና የመገምገም ችሎታ በትምህርት ቤቶች ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋቸዋል። ይህም ውጤታማ የመማር ማስተማር ፕሮግራሞችና የትምህርት ቤቶች አገልግሎቶች እቅድ ዝግጅትን ለመደገፍ ያስችላቸዋል። በውሳኔዎች የቤተሰቦችና የሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፣ ውጤታማና ተገቢ ተግባቦቶች መኖር ለትምህርት ቤቶች የማህበረሰቡ ድጋፍ ቀጣይነትን ለማረጋገጥ እንደሚረዳ መረዳት ይኖርባቸዋል።

## 3. የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ አደረጃጀት

የሱፐርቫይዘሮች ስታንዳርድ 6 የሙያዊ ብቃት ስታንደርዶችን እንዲያካትት ሆኖ ተዘጋጅቷል። እነዚህ 6 የሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶች ለትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ከሚያስፈልጉ አራት ሙያዊ ርዕሰ ጉዳዮች የመነጩ ናቸው። እነሱም ራዕይና እሴቶች፤ የግል ባህሪያት ዓይነትና ማህባራዊና የግንኙነት ክህሎቶች፤ ሙያዊ እውቀትና ግንዛቤ እና ሙያዊ የተግባራት ክንውን ናቸው። እያንዳንዱ የሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ ይዘትንና ተዛማጅ የክንውን ውጤቶችን የሚያስረዳ መግለጫን አስከትሏል። የተወሰኑ ሙያዊ ተግባራትን የሚያሳዩና እያንዳንዱን ስታንዳርድ የገነቡ 26 የሚሆኑ ንዑሳን ስታንዳርደች ተካቷል። የተወሰኑ የክንውን ደረጃዎችን ለመመዘን እንዲቻል የሚፈለጉ በህሪያትንና ክንውኖችን ለማየት የሚያስችሉ 141 አመላካቾችም ከነዚህ ስታንዳርዶች አኳያ ተለይተዋል። ይህም ዋናና ንዑሳን ስታንዳርዶችንና አመላካቾችን ከአራቱ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ የእድገት ደረጃዎች (ጀማሪ ፣ ብቁ 1፣ ብቁ 2ና መሪ ) ጋር በማናበብ ወይም በማቀናጀት ተከናውኖ በአባሪ 2ና 3 በዝርዝር እንዲቀመጥ ተደርጓል። ለትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች የሚያስፈልጉ አራቱ ሙያዊ ርዕሰ ጉዳዮች፣ የሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶች፣ የክንውን አመላካቾችና አራቱ የሙያዊ እድገት ደረጃዎችም በዚህ ሰነድ በሚቀጥሉት ክፍሎች የሚብራሩ ሲሆን አባሪዎቹም ተያይዘዋል።

### 3.1 ለትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች የሚያስፈልጉ ሙያዊ ርዕሰ ጉዳዮች

ለትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች የሚያስፈልጉ ሙያዊ ርዕሰ ጉዳዮች ማለትም ራዕይና እሴቶች፣ የግላዊ ባህርይ ዓይነቶች፣ ማህበራዊና ግላዊ የግንኙነት ክህሎቶች፤ እውቀትና ግንዛቤ እንደዚሁም ሙያዊ የተግባራት ክንውን ለአረዳድ እንዲመች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። ተዘጋጅተው የቀረቡት የሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶችም ከነዚህ አራት

የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ርዕሰ ጉዳዮች የመነጩ እንደመሆናቸው መጠን የተገናኙና የተያያዙ ናቸው። በእርግጥ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ተግባራት በአጠቃለይ በእነዚህ አራት ሙያዊ ርዕሰ ጉዳዮች ይመራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ እያንዳንዱ የሙያ ብቃት ስታንዳርድ ከነዚህ **አራት አስፈላጊ ርዕሰ ጉዳዮች** ጋር ተያያዥነትም አለው።.

### 3.1.1 ራዕይና እሴቶች

የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ከሁሉም በላይ የሚፈለጉት የትምህርት ቤቶች ራዕይና ስትራቴጂያዊ እቅድ ዝግጅትን ለመደገፍ ነው። **ፍትሓዊነትን፣ ሰብዓዊነትንና ልዩነትን ማክበር፣ ሥነምግባራዊና ዲሞክራሲያዊ አሠራርን መከተል፣ የእድሜ ልክ ትምህርትን መደገፍ በሚሉና በመሳሰሉ እሴቶች በመመራት የወጣቶችንና የጎልማሶችን ትምህርትና እድገትን ለመደገፍ ቁርጠኞች መሆን ያስፈልጋቸዋል**። ከስትራቴጂያዊ ራዕይ፣ ከትምህርት ባህል፣ ልማድና ሁሉም ትምህርት ቤቶች ለማሳደግ ከሚፈልጉት አዎንታዊ ፍልስፍና የምንጸባረቁ የማህበረሰቡ ምርጥ ምርጫዎችን መረዳት፣ መምራት ማስታረቅና ማገልገል አለባቸው። ለሁሉም ትምህርት ቤት ማህበረሰብ ከፍተኛ ስታንዳርድን በጥብቅ በመያዝ ክብራቸውን ለማሳደግ መቻልም አለባቸው።

### 3.1.2 የግላዊ በህርይ ዓይነቶችና ማህበራዊና የግንኙነት ክህሎቶች

ይህ ለትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያ ተፈላጊ የሆነው ርዕሰ ጉዳይ **ለስሜታዊ የአእምሮ እምቅ ችሎታ፣ ለግንዛቤ፣ ለተለማጭነትና በትምህርት ቤትና ማህበረሰቡ አመራርና አስተዳደር ውስጥ ለግላዊ ደህንነት ጠቀሜታ እውቅና ይሰጣል።** የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች የአመራርና የአስተዳደር አቀራረቦቻቸውን ከተጨባጩ ሁኔታ ጋር ለማስማማት **የተግባር ክንውኖቻቸውን በየጊዜው በመገምገም ለውጦችን መተግበር ይጠበቅባቸዋል። ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ቅራኔዎችን ለማስታረቅ ራሳቸውን በትክክል በመያዝና ትህትና በተሞላበት ሁኔታ ማህበራዊ ክህሎቶችን መጠቀም ያስፈልጋቸዋል።** ለተማሪዎችና ለሥራ ቡድኖች **በሚሠሩበት ትምህርት ቤት ማበረሰብ ውስጥ ለትምህርት ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር በሁሉም የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ዘንድ እምነትን ማዳበር መቻልም አለባቸው።**

### 3.1.3 እውቀትና ግንዛቤ

የትምህርት በት ሱፐርቫይዘሮች የወቅቱን የአመራርና የአስተዳደር ተግባራዊ ልምድና ንድፈ ሃሳብን በማወቅ እውቀታቸውን ለትምህርት ቤት መሻሻል ጥቅም ላይ ማዋል አለባቸው። ዘመናዊ ጥናትና ምርምርና ፔዳጎጂን፣ ሥርዓተ ትምህርትን፣ ምዘናንና ውጤት የማሳወቅ ሂደትን አስመልክቶ ከታዩ መሻሻሎች ጋር የተዋወቁ መሆን ይኖርባቸዋል። **ተገቢ የብሔራዊ እድገት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ የአሠራሮችና የተነሳሺነት እንደዚሁም ተገቢ የፌዴራልና የክልል መንግታት አዋጆችና ስምምነቶች እውቀቶችንም ሊኖራቸው ይገባል።**

የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች በትምህርታዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ውስጥ የትምህርት ቤት ማህበረሰብን ፍላጎቶች ለማርካት **ሙያዊ እውቀታቸውን በመጠቀም ጥናትና ምርምር ማካሄድ መቻል ይጠበቅባቸዋል።** የትምህርት ቤት ተጨባጭ ሁኔታዎችንና ሁኔታዎቹ በተማሪዎች ተከታታይ ትምህርት ላይ እንዴት ተፅዕኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉ ማወቅም አለባቸው። የትምህርት ቤት ተማሪዎችን አካላዊ፣ ማህበራዊና አእምሮአዊ እድገትና ጠባያት ለመደገፍ እውቀታቸውንና ክህሎቶቻቸውን እንዴት እንደሚያደራጁ ማሳየት መቻል አለባቸው። .

### 3.1.4 የሙያዊ ተግባራት ክንውን

የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች **በትምህርት ቤቶች ለመማር-ማስተማር ውጤታማነት አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠር በማበረታታት መደገፍ መቻል ይኖርባቸዋል።** ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ሁሉንም ያካተተና በመፈታተን የሚያሠራ (Challenging) የመማሪያ አካባቢን በመፍጠርና በመጠበቅ ፍትሐዊ የባሕርይ አያያዝና አስተዳደር ሥርዓትን በማበረታታት መደገፍ መቻልም ይጠበቅባቸዋል። የውጤታማ ሱፐርቭዥን ሥራ ስተራቴጂዎች ክምችት ኖሮአቸው በትክክል በተቀየሰ የድጋፍ፣ የቁጥጥርና የግምገማ ፕሮግራሞች ትግበራ ላይ ለመጠቀም እንዲችሉ **ቀላልና ተገቢ የተግባቦት ቴክኒኮችን ሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋቸዋል።** ከታች ወደ ላይ ከትምህርት ቤቶች እስከ ትምህርት ሚኒስቴር ከላይ ወደ ታች ከትምህርት ሚኒስቴርን እስከ ትምህርት ቤቶች ባሉ የሃላፊነት እርከኖች መካካል እንደዚሁም **በትምህርት ቤቶችና በማበረሰቡ መካካል ተግባቦቶችን በመፍጠር ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል።** የትምህርት ቤቶች ማህበረሰቦች ፈላጎቶችን በማርካት ላይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ **የአሠራሮቻቸውን ገጽታ በየጊዜው መገምገም ይኖርባቸዋል።**

## 3.2 የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶች

ይህ ክፍል ስድስቱን የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶችን ይገልጻል። ስድስቱም የሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶች ለትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያ ከሚያስፈልጉና ከዚህ በላይ ከተገለፁ ከአራቱ ሙያዊ ርዕሰ ጉዳዮች አንጻር ከሱፐርቫይዘሮቹ የሚጠበቅባቸውን የሚለዩ ናቸው። እያንዳንዱ ስታንዳርድ በየሙያዊ ብቃት ደረጃ ስኬትን የሚያመላክቱ አመላካቾችን ያቀፉና የተለያዩ ቀጥር ያላቸው ንዑሳን ስታንዳርዶችን አካቷል። የሚመለከታቸው ሱፐርቫይዘሮችም በተጨባጩ የሥራ ቦታቸው እንደ ሙያዊ የእድገት ደረጃቸው የሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶቹን በተግባር በማሳየት የሚጠበቅባቸውን ማንፀባረቅ ይኖርባቸዋል።

### 3.2.1 ስታንዳርድ 1፦ በሙያዊ የተግባራት ክንውን ሂደት ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለኑሮ በመማር ለሕይወት ሙሉ ትምህርት አርአያ ሆኖ ማነቃቃት፣

**መግለጫ**

ይህ ስታንዳርድ የመማር-ማስተማር ጥራትንና በትምህርት ቤት የሚሰጠውን ትምህርት ለማሻሻል የሚያስችል ሙያዊ አመራር ለመስጠት የሚያስፈልጉ እውቀት፣ ክህሎትና የሚጠበቁ የክንውን ውጤቶችን ይገልጻል። በቅንጅት በጋራ ተዘጋጅቶና በትክክል ግልጽ

ተደርጎ የተቀመጠውን ራዕይ መሠረት በማድረግ ትምህርት ቤቶች መማርን የስትራቴጂክ እቅድ ዋነኛ አካል እንዲያደርጉ ማስቻልንም ያጠቃልላል። በመሆኑም በመማር ስትራቴጂ ዝግጅትና ትግበራ ሂደት ከፍተኛ ስታንዳርድን በመጠበቅ የአመራር ድጋፍ ለሚሰጡ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ተገቢ ነው። ለትምህርት ቤቶች መሻሻል በትምህርት ቤት መማርና እድገትን በመከታተልና የትምህርት ቤት ስትራቴጂ ቅርጽን በመገምገም ሂደት በተግባር ላይ ለታየ የሱፐርቫይዘሮች ችሎታም ይሠራል።

### ንዑሳን ስታንዳርዶች

የተለያዩ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ከስታንዳርድ አንድ ጋር በተዛመደ ሁኔታ በሱፐርቪዥን ሥራዎቻቸው ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ እውቀታቸውን፣ ክህሎቶቻቸውንና ግላዊ ተዋጽኦዎቻቸውን በጥቅም ላይ ለማዋል የሚተጉባቸው ተግባራት ናቸው። የክንውን ደረጃቸውን የሚያመለክቱ አመላካቾችንም አካተው ይዘዋል። እነዚህም ንዑሳን ስታንዳርዶች፦

1.1 መማርን የስትራቴጂክ እቅድ ማዕከል አድርጎ ማስቀመጥ፣
1.2 ከፍተኛ ስታንዳርዶችን ማስቀመጥ፤
1.3 በትምህርት ቤት በመማር ስትራቴጂ ዝግጅት ሂደት የአመራር ድጋፍ መስጠት፣
1.4 በትምህርት ቤት የመማር ስትራቴጂ ትግበራን ማረጋገጥ፣
1.5 በትምህርት ቤት መማርና እድገትን መገምገም ናቸው።

## 3.2.2 ስታንዳርድ 2፦ ለትምህርታዊ ጥናትና ምርምር ትምህርት ቤቶችን ማነሳሳት፣ ማካሄድና መምራት

### መግለጫ

ይህ ስታንዳርድ በትምህርት ቤት ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ በስትራቴጂክ ክንውኖችና ውጤቶች ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ለማሳደርና የጥናትና ምርምር ተግባራትን ለማበረታታት በማቀድ በመተግበርና ሪፖርት በማድረግ ግንዛቤን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ እውቀት፣ ክህሎትና የሚጠበቁ የክንውን ውጤቶችን ይገልጻል። ስታንዳርዱ የትምህርታዊ የጥናትና ምርምር ስትራቴጂ ማዘጋጀትን፣ የተለያዩ የትምህርታዊ ጥናትና ምርምር ቴክኒኮች መጠቀምንና መረጃዎችን በመፈተሽና በመገምገም ግኝቶችን ማቅረብን ያጠቃልላል። መማር የግለሰቦች፣ የቡድንና የትምህርት ቤቶችን የተግባራት ክንውን ለማሳደግ እንደሚችል ለማረጋገጥ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ጥናትና ምርምርን የመጠቀም አቅምንም ይመለከታል።

ለዚህም የሚታሰበው የትምህርታዊ ጥናትና ምርምር ዓላማና አቀራረብ በተለያዩ የትምህርት ቤቶች ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ መሠረት የስታንዳርዱ ትኩረት የትምህርት ቤት ውጤቶችን ለማሻሻል በትምህርታዊ ጥናትና ምርምር ላይ ይሆናል። የእድገት አቅምንና ከመማር ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ተግባራት ለማሳደግ ጥራት ያለው መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ የተለያዩ የጥናትና ምርምር ተግባራትንና ቴክኒኮችን መምራትንም ያቅፋል።

### ንዑሳን ስታንዳርዶች

ስታንዳርድ ሁለትን በተመለከተ በሱፐርቫዥን ሥራ አካባቢ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ እውቀታቸውን ክህሎቶቻቸውንና ግላዊ ተዋጽኦዎቻቸውን ተግባራዊ በሚያድረጉበት ወቅት እንዲተጉባቸው የሚጠበቅባቸው ተግባራት ናቸው። እነዚህም የክንውን ደረጃቸውን የሚያመለክቱ አመላካቾችን ያካተቱ ሆነው የሚከተሉትን የሙያዊ ተግባራት ስብስብ ያጠቃልሉ።

2.1 ትምህርታዊ የጥናትና ምርምር ስትራቴጂን በማዘጋጀት የትምህርት ቤት መምህራንንና ርዕሰ መምህራንን ማነሳሳት፣ መደገፍና መምራት፣

2.2 የትምህርት ቤት መምህራንና ርዕሰ መምህራን የተለያዩ የጥናትና ምርምር ቴክኒኮችን በመምረጥ ለመጠቀም እንዲችሉ መደገፍ፣

2.3 የትምህርት ቤት መምህራንና ርዕሰ መምህራን መረጃን በመመርመር ግኝቶችን ለማቅረብ እንዲችሉ መደገፍ፤

### 3.2.3 ስታንዳርድ 3፡- በትምህርታዊ ተግባራት ክንውኖች ሂደት ወቅታዊ እውቀትንና ግንዛቤን ጥቅም ላይ ማዋል።

**መግለጫ**

ይህ ስታንዳርድ በመማር-ማስተማር ተግባራት ክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ቁጥጥር ሂደት የአመራርና የአስተዳደር ጽንሰ ሃሳቦችንና አሠራሮችን ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ እውቀት፣ ክህሎትና የሚጠበቁ የክንውን ውጤቶችን ይገልጻል። በትምህርት ቤት ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ የመማር ስትራቴጂዎች መሻሻልን የሚደግፉ የላቁ የመማር ተግባራት ክንውኖችን በማነሳሳት ለመተግበር የሚያስችሉ እውቀት፣ ክህሎትና የሚጠበቁ የክንውን ውጤቶችንም ጨምሮ ያብራራል። ስታንዳርዱ፡-

- ትምህርት ቤቶች አደረጃጀቶቻቸውንና አሠራሮቻቸውን ለመቀየስ፣ ሕግና ደንብ የሚጠይቅባቸውን ለማሟላት፣ አገልግሎቶቻቸውንና ፕሮፋይሎቻቸውን ለመምሥረት እንዲችሉ ማብቃትንና
- ትምህርት ቤቶች የመማር-ማስተማር ተግባራት ክንውኖቻቸውን እንዲያሻሽሉ ለመደገፍ ወቅታዊ የትምህርት ቤት የተግባራት ክንውኖች ግምገማ ማከናወንን ያካትታል።

ትምህርት ቤቶች መማር-ማስተማርን ለማሻሻልና የተሻሻሉ የመማር ተግባራት ክንውኖች አቀበባልን በመፈተሽ አቀባበሉንና ትግበራውን ለማሳለጥ እንዲችሉ ለማገዝ ያለውን ወቅታዊ ስትራቴጂ መገምገምን ይጨምራል። በአጠቃላይ ስታንዳርድ ሦስት የትምህርት ቤት አመራርና አስተዳደር መሻሻልን ያበረታታል፤ ይደግፋል። የትምህርት ቤቶች ውጤታማነትን ለመደገፍ ተገቢ አስተያየቶችን (ግብረ መልሶችን) ባካተቱ የግምገማ ውጤቶች የሚጠቃለልም ይሆናል።

## ንዑሳን ስታንዳርዶች

ስታንዳርድ ሦስትን በተመለከተ በሱፐርቫዥን ሥራ አካባቢ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ እውቀታቸውን፣ ክህሎቶቻቸውንና የግል ሙያዊ ተዋጽኦዎቻቸውን

ተግባራዊ በሚያድረጉበት ወቅት እንዲተጉባቸው የሚጠበቅባቸው የተለያዩ ሙያዊ ተግባራት የሚከተሉት ሆነው የክንውን ደረጃቸውን የሚያመለክቱ አመላካቾችን ያካተቱ አካትተዋል።

3.1 ትምህርት ቤቶች የመማር ተግባራት ክንውኖችን እንዲያሻሽሉ ለመደገፍ የወቅቱን የትምህርታዊ ተግባራት ክንውኖችን መገምገም፣
3.2 ትምህርት ቤቶች የተሻሻሉ የመማር ክንውኖችን በመቀበል፣ በማስማማትና የራሳቸውን አደረጃጀቶችና አሠራሮችን በመቀየስ እንዲተገብሩ ማስቻል፣
3.3 ውጤታማ የትምህርት ቤት አገልግሎቶችን በማበረታታት መምራት፣
3.4 ለትምህርት ቤቶች መሻሻል ተገቢ ግብረመልሶችንና ድጋፎችን ለመስጠት የክትትልና ግምገማ ፕሮግራምን በማቀድ ማዘጋጀት፣

### 3.2.4 ስታንዳርድ 4፡- ውጤታማና አሳታፊ የትምህርት ቤት አመራርና አስተዳደርን መተግበር

**መግለጫ**

ስታንዳርድ አራት ውጤታማና አሳታፊ የትምህርት ቤት አመራርና አስተዳርን በማረጋገጥ ለመተግበር የሚያስችሉ እውቀት፣ ክህሎትና የሚጠበቁ የክንውን ውጤቶችን ይመለከታል። ለለውጥ አስተዳደርና አያያዝ እውቅና ለመስጠት በስትራቴጂያዊ ለውጥ አስፈላጊነትና ለለውጥ ስለአሉ እድሎች አስተያየቶችን ይሰጣል። ከዚህም በተጨማሪ ስታንዳርዱ፡-

- የፈጠራ ተግባራት ክንውኖች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለመደገፍ የሚያስችል አካባቢን ለመፍጠር በትምህርት ቤቶች ፈጠራን በመደገፍ የሚያበረታታ አዲስ ሥርዓት መምሥረትን፣
- አስተማማኝ የፈጠራ ተግበራትን ለመምራት የፈጠራ አስተሳሰቦችንና ችሎታን ማመንጨትን፣
- የፈጠራ ባህል መደገፍን፣
- ለፈጠራ አስተሳሰብና ክንውን አስተማማኝ አቀራረብን መጠበቅና የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራንን በልዩነቶች አያያዝና ግምገማ ስትራቴጂዎች ዝግጅትና ትግበራ ላይ መደገፍን ያካትታል።

## ንዑሳን ስታንዳርዶች

ስታንዳርድ አራትን በተመለከተ በሱፐርቭዥን ሥራ አካባቢ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ እውቀታቸውን፣ ክህሎቶቻቸውንና የግል ሙያዊ ተዋጽኦዎቻቸውን ተግባራዊ በሚያድረጉበት ወቅት እንዲተጉባቸው የሚጠበቅባቸው የተለያዩ ሙያዊ ተግባራት የሚከተሉት ሆነው የክንውን ደረጃቸውን የሚያመለክቱ አመላካቾችን ያካተቱ ናቸው።

4.1 ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደት አመራር ለማረጋገጥ ለመምህራን ድጋፍ መስጠት፣
4.2 ውጤታማና አሳታፊ የትምህርት ቤት አስተዳደርን ማረጋገጥ፣
4.3 ተገቢ የተማሪዎች ልዩነቶች አስተዳደርና አያያዝ ሥርዓት እንዲኖራቸው ለትምህርት ቤቶች ድጋፍ መስጠት፣
4.4 በለውጥ አስተዳደርና አያያዝ የስትራቴጂያዊ ለውጥ አስፈላጊነትንና ለለውጡ ያሉ እድሎችን በሚመለከት ሃሳቦችን ወይም አስተያየቶችን መስጠት፣

## 4.5 መሻሻልን፣ ፈጠራንና ለውጥን መምራት፤

### 3.2.5 ስታንዳርድ 5፦ በትምህርት ቤቶች ሊሟሉ የሚገቡ አስፈላጊ ሁኔታዎችን መለየትና መተርጎም

**መግለጫ**

ይህ ስታንዳርድ የትምህርት ቤቶች ሥራና የአሠራር ስፋትን ወይም መጠንን ግልጽ ለማድረግ፣ ከውስጥና ከውጪ በትምህርት ቤቶች ሊሟሉ የሚገቡ የተለያዩ ሁኔታዎችንና ግዴታዎችን ለመለየትና ለመተርጎም የሚያስችሉ እውቀት፣ ክህሎትና የሚጠበቁ የክንውን ውጤቶችን ይመለከታል።

**ንዑሳን ስታንዳርዶች**

ስታንዳርድ አምስትን በተመለከተ በሱፐርቭዥን ሥራ አካባቢ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ እውቀታቸውን፣ ክህሎቶቻቸውንና የግል ሙያዊ ተዋጽኦዎቻቸውን ተግባራዊ በሚያድረጉበት ወቅት እንዲተጉባቸው የሚጠበቅባቸው የተለያዩ ሙያዊ ተግባራት የሚከተሉት ሆነው የክንውን ደረጃቸውን የሚያመለክቱ አመላካቾችን ያካተቱ ናቸው።

- 5.1 የትምህርት ቤት ሥራና አሠራር ስፋትን ወይም መጠንን ግልጽ ማድረግ
- 5.2 ትምህርት ቤቶች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ሁኔታዎችን መለየት፣
- 5.3 የተለዩ ትምህርት ቤቶች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ሁኔታዎችን መተርጎም፣ መፈተሽና ቅደም ተከተል ማስያዝ
- 5.4 በትምህርት ቤቶች ሊሟሉ የሚገቡ ሁኔታዎችን በመመዝገብ በሰነድነት መያዝ፣

### 3.2.6 ስታንዳርድ 6፦ ራስን፣ ግለሰብንና ቡድንን መገንባት

**መግለጫ**

ይህ ስታንዳርድ የግለሰብንና የቡድን አቅም ግንበታ ፍላጎቶችን በመለየት ሥራና መማር በሚጣመርበት ቦታ የመማሪያ አካባቢ እድገትን ለማበረታታትና ለመደገፍ የሚያስፈልጉ እውቀት፣ ክህሎትና የሚጠበቁ የክንውን ውጤቶችን ይገልጻል። ልዩ ትኩረቱም የራስ፣ የግለሰቦችና የቡድን መማርን (የሥራ ቡድን እድገትን) ለማመቻቸትና ለመደገፍ እንደዚሁም በትምህርት ቤቶች የመማር ክንውንን በመከታተል ለማሻሻል እንዲቻል በስትራቴጂዎች ዝግጅት ላይ ነው።

## ንዑሳን ስታንዳርዶች

ስታንዳርድ ስድስትን በተመለከተ በሱፐርቭዥን ሥራ አካባቢ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ እውቀታቸውን፣ ክህሎቶቻቸውንና የግል ሙያዊ ተዋጽኦዎቻቸውን ተግባራዊ በሚያድረጉበት ወቅት እንዲተጉባቸው የሚጠበቅባቸው የተለያዩ ሙያዊ ተግባራት የሚከተሉት ሆነው የክንውን ደረጃቸውን የሚያመለክቱ አመላካቾችን አካተዋል።

- 6.1 የግለሰብና የቡድን የመማርና እድገት ፍላጎቶችን መለየት፣
- 6.2 ግቦችን በማስቀመጥ ለራስና ለሌሎች እድገት ሃላፊነት መውሰድ፣
- 6.3 ለራስ፣ ለግለሰቦችና ለቡድን ለሙያዊ ትምህርት እድሎችን መፍጠር
- 6.4 ለራስ፣ ለግለሰቦችና ለቡድን ሙያዊ ትምህርትን በማመቻቸት ማበረታታት

### 6.5 በመከታተልና በመገምገም የመማር ውጤታማነትን ማሻሻል።

## 3.3 የክንውን አመላካቾች

የክንውን አመላካቾች በየእያንዳንዱ ሙያዊ ደረጃ ወይም ስታንዳርድ የሱፐርቫዥን ድጋፍ የጥራት ይዘቶችን ወይም ክፍሎችን ይለያሉ። ከስምምነት የተደረሰባቸው የድጋፍ አሰጣጥ ውስብስብ ሂደቶች ጠበያትን አካትተው ይይዛሉ። አንድ ውጤታማና ስኬታማ ሱፐርቫይዘር መማር ዋጋ እንዲኖረው በእያንዳንዱ ስታንዳርድ መግለጫዎች በዝርዝር በተቀመጠው መሠረት አመቺ አካባቢዎችን በመፍጠርና እውቀቶቹን በማቀናጀት በሙያዊ ተሳትፎዎቹና አሠራሮቹ ሂደት ተግባራዊ እንዲያደርግ ይጠበቃል።

## 3.4 አራቱ የሱፐርቫይዘሮች የሙያዊ እድገት ደረጃዎችና ችሎታዎች

በዚህ በትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ ውስጥ አራቱ የሙያዊ እድገት ደረጃዎች በሙያዊ ተግበራት ክንውናቸው ሂደት ስታንዳርዶቹን ላሚሉና ችሎታውን ላላቸው ሱፐርቫይዘሮች እውቅናን ለማመልከት የሚሰጡ የሙያ እድገት ዕድሎች ናቸው። እያደጉ የሚሄዱ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች እውቀት፣ የተግባራት ክንውንና ተሳትፎ ደረጃዎችንም ይወክላሉ። በደረጃዎቹ ውስጥ ማለፍ ከግንዛቤና እውቀት፣ ከንድፍ ሃሳቦችና ልምዶች ወይም ተሞክሮ ትግበራ ክህሎት፣ ውስብስብነታቸው እየጨመረ ከሚሄድ የተለያዩ ውስብስብ አካባቢዎች ውስጥ ሙያዊ በሕሪያትንና ሥነምግባርን ከማሻሻል ጋር ተዛማጅነት ካላቸው እድገቶችና ከፍተኛ ግምት ከተሰጣቸው የተግባራት ክንውኖች ጋር ተያይዟል። እነዚህ አራቱ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ እድገት ደረጃዎች ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል።

### 3.4.1 ጀማሪ ሱፐርቫይዘሮች

ጀማሪ ሱፐርቫይዘሮች በመምህርነት፣ በትምህርት ክፍል ሃላፊነት፣ በዩኒት መሪነትና ወይም በትምህርት ቤት ርዕሰ መምህርነት በመሥራት በግምት ውስጥ ሊያዝ የሚችል የትምህርት ቤት ልምድና ተሞክሮ እንዲኖራቸው ይጠበቅባቸዋል። እንደ ትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች የሚፈለግባቸውን የመነሻ ትምህርትና ሥልጠና በመውሰድ የሚጠበቅባቸውን አካዳሚክ ደረጃ ማሟላትም ይኖርባቸዋል። እነዚህ ሱፐርቫይዘሮች በትምህርት ቤቶች የመማር-ማስተማር ሂደትን ለመከታተል የሚያስችል መሠረታዊ እውቀትና ክህሎት ይኖራቸዋል። የትምህርት ቤት ውጤቶችን ለማሻሻል የሙያዊ አመራር ሚናቸውንና ሃላፊነታቸውን እንደዚሁም ወቅታዊና ተገቢ ግብረመልሶችን እንዴት መርጠው መስጠት እንዳለባቸውም ይረዳሉ።

ጀማሪ ሱፐርቫይዘሮች ለትምህርት ቤቶች መሻሻል በስትራቴጂክ እቅዶች ዝግጅትና ትግበራ ትምህርት ቤቶችን መደገፍ ይችላሉ። የትምህርት ቤቶች መሻሻል ፕሮግራሞችን ለመደገፍ ከትምህርት ቤት ማህበረሰቦች ጋር ግንኙነቶችን በመፍጠር ስለትራቴጂዎቹ ትግበራ ያላቸውን እውቀት ማሳየት ይችላሉ። የተማሪዎች ውጤቶችን ለማሳደግ በትምህርት ቤቶች ድጋፍ አሰጣጥ ሂደት ከትምህርት ቤት ማህበረሰብ ጋር የመሥራት አቅማቸውን ማሳየትም

ይኖርባቸዋል። በተገቢ ሥነምግባርና በቅንጅት ከሥራ ባልደረቦችና ከትምህርት ቤት ማህበረብ ጋር የመሥራት ጠቀሜታን ይረዳሉ።

### 3.4.2 ብቁ 1 የተምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች

ከጀማሪ ሱፐርቫይዘሮች የሚጠበቀውን ሁሉ ከማሟላት በተጨማሪ ብቁ 1 ሱፐርቫይዘሮች ለትምህርት ቤት መምህራንና ርዕሰ መምህራን ውጤታማ ድጋፎችን መፍጠር ይጠበቅባቸዋል። ፍላጎቶችን በመመዘን ድጋፎቻቸውን ከፍላጎቶቹ ጋር ማስማማት መቻል አለባቸው። በዚህ ደረጃ ያሉ ሱፐርቫይዘሮች በሙያቸው ንቁ ተሳታፊ እንደመሆናቸው መጠን ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመተባበር የራሳቸውን ሙያዊ የመማር ፍላጎቶችን መለየት፣ ማቀድና መገምገም ይችላሉ። እንደ ቡድን አባላት ከሥራ ባልደረቦች ጋር በቅንጅት መሥራት ይችላሉ፤ በሙያዊ ክንውናቸው ላይ ተፅዕኖ በሚያሳድሩ ትምህርታዊ ጉዳዮች ላይ ምክር ወይም ድጋፍ ለመስጠት ይጥራሉ። በሁሉም የምክክር መድረኮች በተገቢ ሙያዊ ሥነ ምግባር ይሳተፋሉ። እነዚህ ሱፐርቫይዘሮች እውቀት ያላቸውና ከትምህርት ቤቶች ጋር የሚሠሩ ባለሙያዎች ንቁ አባላት ናቸው።

በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች በክህሎታቸውና በውጤታማ ተለማማጅነታቸው እውቅና አላቸው። በመሆኑም የሥራ ባልደረቦቻቸውንና የራሳቸውን ተግባራዊ ክንውኖች ለማሻሻል ሁልጊዜ በግልና በቅንጅት ይሠራሉ። ለሥራ ባልደረቦቻቸው ትምህርታዊ አስተዋጽኦ ለማድረግ ችሎታውንና ክህሎቱን አላቸው። ሌሎችን የመምከርና የመምራት ሚና መጨወትም ይችላሉ። በትምህርት ቤቶች ትምህርታዊ ውጤቶችን ለማሻሻል ሁልጊዜ ስለውጤታማ የማስተማር ተግባር ውይይቶችን በማነሳሳትና በማስጀመር ይሳተፋሉ። አዎንታዊና ምርታማ የመማሪያ አካባቢን ለመፍጠር መምህራንን ጨምሮ ለሥራ ባልደረቦችና ለርዕሰ መምህራን ስትራቴጂዎችን በማበርከት ይደግፋሉ።

### 3.4.3 ብቁ 2 የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱ ሁለቱ ደረጃዎች የሚጠበቁትን ጨምሮ በብቁ 2 ደረጃ ላይ ያሉ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች በሙያዊ ደረጃቸው የትምህርት ቤት ሱፐርቭዥን ንድፈ ሃሳቦችንና ልምዶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ጥልቅ እውቀትና ሊታይ የሚችል ክህሎት እንዲኖራቸው ይጠበቅባቸዋል። በመምህራንና በአስተዳደር አካላት፣ በመምህራንና ተማሪዎች፣ በተማሪዎችና በአስተዳደር አካላት፣ በተማሪዎች በራሳቸው፣ በትምህርት ቤት ማህበረሰብ እንደዚሁም በትምህርት ቤቶች፣ በወላጆችና በሰፊው ህብረተሰብ መካከል ስኬታማና ውጤታማ የቡድን ሥራ ባህልና መንፈስን መፍጠር ይኖርባቸዋል።

የፖሊሲ፤ የስትራቴጂዎችና የፕሮግራሞች ትግበራን በማመቻቸት ትልቁን ሚና መጫወትም አለባቸው። በደረጃቸው በሱፐርቭዥን ተግባራት ክንውን አርአያ መሆን ይኖርባቸዋል። የተማሪዎች ውጤቶችን ለማሻሻል የመማር-ማስተማር ሂደቶችን ለማቀድ ለመገምገምና ለማሻሻል ከሥራ ባልደረቦች ጋር ይሠራሉ። በትምህርት አዳዲስ የእድገት ውጤቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባሉ። በትምህርት ቤቶች የመማር-ማስተማር ሂደትን ለማሻሻል የትምህርት ቤቶች የምዘና መረጃን በመፈተሽ ይጠቀማሉ። ለሥራ ባልደረቦች ሙያዊ

ትምህርትንና የልምድ ልውውጥ እድሎችን ከፍ የሚያደርግ አካባቢን ለመምሥረት ወይም ለመፍጠርም ንቁ ናቸው። የራሳቸውን የሙያዊ ትምህርት ፍላጎቶችን በመከታተል ከትምህርት ቤት ፍላጎቶች ጋር ያስኬዳሉ። ሁልጊዜ ተገቢ ሥነምግባርን ያንፀባርቃሉ። በመሆኑም የራሳቸው ግላዊና የማህበራዊ ተግባቦት ክህሎቶች በከፍተኛ ደረጃ አድጓል።

## 3.4.4 መሪ ሱፐርቫይዘሮች

ከዚህ በላይ በተገለፁ ሦስት ደረጃዎች ሁሉ ውስጥ ከመሠረታዊ እስከ ከፍተኛ ችሎታዎች ጋር ያለፉ በመሆናቸው መሪ ሱፐርቫይዘሮች የተከበሩና በከፍተኛ ደረጃ እውቅና ያገኙ ባለሙያዎች ናቸው። ከሥራ ባልደረቦች፣ ከትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን፣ ከመምህራን ከወላጆች፣ ከትምህርት ቤት ማህበረሰብና ከአጠቃላይ ህብረተሰቡ ጋር አክብሮት የተሞላበትና ውጤታማ የሆኑ ተግባቦቶችን ፈጥሮአል። ሁልጊዜ በፈጠራ የታጀበ አስተማማኝ የአመራር ተግባራት ክንውኖችን ማሳየት ይችላሉ። ለሁሉም የሥራ ባልደረቦችና ተማሪዎች ትምህርታዊ እድሎችን በማሻሻል ላይ ያተኮሩ ተግበራትን በማነሳሳት ይመራሉ። ለመማር ልዩነቶች ዋጋ በመስጠትና በማክበር የተለያዩ ተማሪዎች ፍላጎቶችን ማርካት የሚችል አካባቢን ለመፍጠር በቀርጠኝነት ይሠራሉ። የራሳቸውን ተግባራዊ ክንውኖችን በማሻሻል ልምዶቻቸውን ለሥራ ባልደረቦቻቸው ለማካፈል ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋሉ። በሥራ ባልደረቦች መካከል የፈጠራ አስተሳሰቦችን በማበረታታት እውቀትን፣ የተግባራት ክንውንንና የሙያዊ ተሳትፎ መንፈስን በሌሎች ውስጥ ለማዳበር ተፈላጊውን ክህሎት አላቸው። ውጤታማ ትምህርትና የትምህርት እድሎችን ለመስጠት በዚህ ደረጃ ያሉ የትምህርት ሱፐርቫይዘሮች ጥልቀት ያለው እውቀት፣ ግንዛቤና ክህሎት ተግባር ላይ ማዋል ይችላሉ።

መሪ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች በትምህርት ቤቶችና በቁልፍ ባለድረሻዎች መካካል ስኬታማና ውጤታማ የአጋርነት ሥርዓት በመፍጠር፣ የፕሮግራሞችን ዘላቂነት የሚያረጋግጡ ስትራቴጂዎችን በማስተዋወቅ፣ ከፖሊሲና ስትራተጂዎች ጋር ጋር ተዛማጅነት ባላቸው ተግባራት ላይ ሥልጠናዎችን በመስጠት፣ የፕሮግራሞች ትግበራ ያስገኛቸው ውጤቶችን አስመልክቶ የተለያዩ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድና በትምህርት ቤቶች አመራር የማህበረሰቡን ተሳትፍ ለማሳደግ አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ለከፍተኛ የሱፐርቭዥን ተግባራት ክንውን ላይ በማተኮር ይሠራሉ። ከወላጆች/አሳዳጊዎች የተገኙ ግብረ መልሶችን ከግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ የተማሪዎች የምዘና መረጃን በመፈተሽ፣ ፕሮግራሞችን በመገምገምና በመከለስ የተማሪዎች ክንውኖችን የማሻሻል ሂደቶችን መምራት ይችላሉ። ይህም በውጤታማ የመማር ማስተማር ላይ ከተደረጉ ወቅታዊ የጥናትና ምርምር ውጤቶች ጋር ተዋህዶ ይታያል። በመሆኑም በዚህ ደረጃ ያሉ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች በማህበረሰቡ ውስጥ ትምህርት ቤቱንና የማስተማር ሙያውን ይወክላሉ። በትምህርት ቤት ሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ የሚፈለገውን ሥነምግባር የተላበሱና የተከበሩ ባለሙያዎችም ሆነው ይታወቃሉ።

## አባሪዎች

### አባሪ 1፦ የሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶች ጥቅል ቻርት

| የሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ፦ የትምህርትቤት ሱፐርቫይዘሮች | | |
|---|---|---|
| ሙያዊ ኮድ፦ | | |
| በሙያዊ የተግባራት ክንውን ሂደት ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለኑሮ በመማር ለሕይወት ሙሉ ትምህርት አርአያ ሆኖ ማነቃቃት | ለትምህርታዊ ጥናትና ምርምር ትምህርት ቤቶችን ማነሳሳት፣ ማካሄድና መምራት | በተግባራዊ የትምህርታዊ ተግባራት ክንውኖች ሂደት ወቅታዊ እውቀትንና ግንዛቤን ሥራ ላይ ማዋል። |
| ውጤታማና አሳታፊ የትምህርት ቤት አመራርና አስተዳደርን መተግበር | በትምህርት ቤቶች ሊሟሉ የሚገቡ አስፈላጊ ሁኔታዎችን መለየትና መተርጎም | ራስን፣ ግለሰብንና ቡድንን መገንባት |

## አባሪ 2፦ የሱፐርቫይዘሮች መሠረታዊ ስታንዳርዶች፣ ንዑሳን ስታንዳርዶችና የክንውን አመላካቾች

## የሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ 1

| የስታንዳርድ ርዕስ | በሙያዊ የተግባራት ክንውን ሂደት ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለኑሮ በመማር ለሕይወት ሙሉ ትምህርት አርአያ ሆኖ ማነቃቃት |
|---|---|
| ስታንዳርድ ኮድ | PCSSSE12A1* |
| ንዑሳን ስታንዳርዶች | የክንውን አመላካቾች |
| 1.1 መማርን የስትራቴጂክ እቅድ ማዕከል አድርጎ ማስቀመጥ | ሀ) የትምህርት ቤቶች ስትራቴጂክ ራዕይና ተልዕኮ ዝግጅትን መደገፍ፣<br>ለ) የትምህርት ቤቶች ስትራቴጂክና ዝርዝር የሥራ እቅዶች ዝግጅትን መደገፍ፣<br>ሐ) የት/ቤቱ ራዕይና እቅዶች ለት/ቤቱ ማህበረሰብና ቁልፍ ባለድርሻዎች ግልጽ እንዲደረጉ መደገፍ፣<br>መ) የት/ቤት ስትራቴጂክ እቅዶች ከባለድርሻዎች ጋር እንዲዳብሩ ት/ቤቶችን መደገፍ፣<br>ሠ) ከፍተኛ የመማር ወጤቶችን ለማስገኘት የሚረዱ የግብ መስኮችን ለመለየት ድጋፍ መስጠት፣<br>ረ) ት/ቤቶች የጋራ የሆኑና ሊለኩ የሚችሉ የት/ቤት ግቦችን በቅንጅት በማስቀመጥ መረጃን መሠረት ያደረገ የክትትል ሥርዓት እንዲፈጥሩ መደገፍ፣<br>ሰ) ከተቀመጠው የጋራ ራዕይና ግብ ስኬት አኳያ የት/ቤት የመሻሻል እርምጃን በሚመለከት መረጃን ለመሰብሰብና ለመፈተሽ ቅንጅታዊ የአሠራርና የአቀራረብ ሥርዓትን መቀየስ፣<br>ሸ) በተከታታይ የመሻሻል ሂደት ላይ ለሚገኘው ተግባቦትና የት/ቤት ስተራቴጂክ እቅድ የአደረጃጀት ሥርዓትን በማዘጋጀት መጠበቅ፣ |
| 1.2 ከፍተኛ ስታንዳርዶችን ማስቀመጥ | ሀ) ለሁሉም ማለትም ለተማሪዎች፣ ለሠራተኞችና ለራስ ከፍተኛ ስታንዳርድ እንዲቀመጥ ሃሳብ መስጠት፣<br>ለ) ተማሪዎች፣ ሠራተኞችና የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ለራሳቸው ከፍ ያለ ስታንዳርድ እንዲያስቀምጡ ማበረታታት፣<br>ሐ) ት/ቤቶች ለት/ቤቱ ማብረሰብ ከፍ ያለ የመማርና የውጤት ግብ እንዲያስቀምጡ መደገፍ፣<br>መ) ት/ቤቶች የተቀመጡ ሰታንዳርዶች ትግበራን ከት/ቤቱ ማህበረሰብ ጋር የጋራ ለማድረግ የተቀመጡ ስታንዳርዶችን ግልጽ በማድረግ እንዲያመቻቹ መደገፍ፣<br>ሠ) ት/ቤቶች ማህበረሰቦቻቸው ከፍተኛ የመማር ውጤቶችን ለማስመዝገብ እንዲችሉ አመቺ ሁኔታን በመፍጠር መደገፍ፣<br>ረ) በት/ቤቶች የውጤቶች ተከታታይ ለውጦችንና መሻሻሎችን በመከታተል ለማበረታታት የክቦሽ መረጃ አሰባሰብና ፍተሻ እንደዚሁም የሙያዊ እድገት ትግበራና ጽብረቃ ሥርዓትን በመቀየስ ማዘጋጀት፣<br>ሰ) የተቀመጡ ስታንዳርዶች ስኬትን ለመከታተል፣ ለመደገፍና ለመገምገም ሥርዓት ያለው አቀራረብና አሠራርን መጠቀም፣ |
| 1.3 በትምህርት ቤት የመማር ስትራቴጂ ዝግጅት ሂደት የአመራር ድጋፍ | ሀ) የት/ቤት ስትራቴጂያዊ ግቦችን ለማሳካት ት/ቤቶች ተለማጭ የመማር ስትራቴጂ እንዲቀይሱ መደገፍ፣<br>ለ) ት/ቤቶች ለመማር ምዘና ስትራቴጂዎችን እንዲያዘጋጁ መደገፍ፣<br>ሐ) የግምገማ ውጤቶችን በመፈተሽ፣ ሪፖርት በማድረግና ከት/ቤቱ ማህበረሰብ ጋር በመወያየት መሻሻሎችን በማስመልከት ግብረ መልሶችንና አስተያየቶችን መስጠት፣<br>መ) በተለማጭ የመማርና የምዘና ስትራቴጂዎች ዝግጅት ላይ ት/ቤቶችን ለመደገፍ ከት/ቤት ስትራቴጂክ ግቦች አኳያ የመማር-ማስተማር አቀራረቦችን መገምገም፣ |

| | |
|---|---|
| መስጠት፣ | ሠ) በተለማጭ የመማርና የምዘና ስተራቴጂዎች ዝግጅት ሂደት በት/ቤት የሚሰጠው ትምህርት ለተወዳደሪነት ስላለው አስተዋጽኦ ከቁልፍ ባለድርሻዎች ጋር በመፈተሽ ማረጋገጥ፣<br>ረ) ት/ቤቶች የመማር ስትራቴጂዎችን ከሰው ሀብትና የመማር ግቦች ጋር እንዲያይዙ በመፈተሽ ማገዝ፣<br>ሰ) የት/ቤት ስትራቴጂክ ፍላጎቶችን ለማርካት በግምገማ ውጤቶች መሠረት ለመማር ማስተማር አቀራረብ መሻሻሎች በሚቀየሱበት ወቅት ድጋፎችን መስጠት፣<br>ሸ) የጥራት አሠራሮችንና ሂደቶችን በመቀየስ ለመጠቀም አማራጮችን መመርመርና መገምገም፣<br>ቀ) የፖሊሲና ስትራቴጂዎች ፍላጎቶችን ለመደገፍ ፍላጎቶቹን በመፈተሽ ለመማር ስትራቴጂዎች ማቀድ፣<br>በ) ከመማር ስትራቴጂ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የቴክኖሎጂ ሥርዓትና ፍላጎቶችን በመፈተሽ ማቀድ፣ |
| 1.4 በትምህርት ቤት የመማር ስትራቴጂ ትግበራን ማረጋገጥ | ሀ) በት/ቤት ተገቢ የመማር ስትራቴጂ ትግበራን በመከታተል ለት/ቤቶች ግብረመልሶችን መስጠት፣<br>ለ) ለመማርና ሰፋ ላለ የሥራ እንቅስቃሴ ፍላጎቶች አስተማማኝ የት/ቤት ምዘና ዘዴዎችንና መሳሪያዎችን ማፅደቅ፣<br>ሐ) ቀጣይነት ላለው ተገቢ የሥራ እንቅስቃሴ ውጤታማነትና ክፍተቶችን በመለየት ግብረመልሶችን ለመስጠት የት/ቤት ስተራቴጂዎችንና አሠራሮችን መገምገም፣<br>መ) ት/ቤቶች የተለዩ ክፍተቶችን ለመሙላት እንድችሉ ስትራቴጂዎችንና አሠራሮችን ማሳደግ፣<br>ሠ) በት/ቤት የመማር ስትራቴጂ አተገባበርን ተከታታይነት ባለው ሁኔታ በመገምገም ስትራቴጂዎቻቸውንና አሠራሮቻቸውን እንዲያድሱ ማገዝ፣ |
| 1.5 በትምህርት ቤት መማርና እድገትን መገምገም | ሀ) በት/ቤት የመማርና እድገት ውጤቶችን በመገምገም ለተሻሉ ውጤቶች ለት/ቤት አሠራሮች መሻሻል አስተያየቶችን መስጠት፣<br>ለ) የመማር ስትራቴጂዎችና ሪሶርሶች በት/ቤት የመማር ግቦችን ምን ያህል እንዳሳኩ ለመከታተል ከት/ባለሙያዎች፣ ከተማሪዎችና ከሌሎች ጋር ለመቀናጀት አሠራሮችን መፍጠር፣<br>ሐ) የተሻሉ የመማር ስትራቴጂዎችና አሠራሮች ትግበራን ለመደገፍ የመማር ስትራቴጂዎችና ሪሶርሶች እንዲሻሻሉ አስተያየት መስጠት፣<br>መ) ለለውጥ እንዲመች አሠራሮችን በመከታተል ግብረ መልሶችን በወቅቱ መስጠት፣ |

PCSSSE12A1*: *በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ2012 የፀደቀ የመጀመሪያ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ 1*

## የሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ 2

| **የስታንዳርድ ርዕስ** | **ለትምህርታዊ ጥናትና ምርምር ትምህርት ቤቶችን ማነሳሳት፣ ማካሄድና መምራት** |
|---|---|
| **ስታንዳርድ ኮድ** | PCSSSE12A2* |
| **ንዑሳን ስታንዳርዶች** | **የክንውን አመላካቾች** |

| | |
|---|---|
| 2.1 ትምህርታዊ የጥናትና ምርምር ስትራቴጂን በማዘጋጀት የትምህርት ቤት መምህራንንና ርዕሰ መምህራንን ማነሳሳት፣ መደገፍና መምራት፣ | ሀ) የትምህርታዊ ጥናትና ምርምር አስፈላጊነትንና የትኩረት ቡድኖችን ፍላጎቶች ግልጽ በማድረግ ማረጋገጥ፣<br>ለ) ተገቢ የጥናትና ምርምር ሥነምግባርና ደንቦችን መገምገም፣<br>ሐ) በመረጃ አስተማማኝነት ላይ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችሉጉዳዮችን መለየትና መፈተሽ፣<br>መ) ሥርዓት ባለው ሁኔታ መረጃን ለመሰብሰብና ለመጠበቅ ዘዴዎችን መፍጠር፣<br>ሠ) የትምህርታዊ ጥናትና ምርምር ስትራቴጂ ማዘጋጀት፣<br>ረ) ያሉ መሳሪያዎችንና ሪሶርሶችን በግምት ውስጥ በማስገባት የጥናትና ምርምር ስትራቴጂ መቀየስ፣<br>ሰ) *የጥናትና ምርምር ስትራቴጂ ትግበራን መከታተል፣ መደገፍና መገምገም፣* |
| 2.2 የትምህርት ቤት መምህራንና ርዕሰ መምህራን የተለያዩ የጥናትና ምርምር ቴኪኒኮችን በመምረጥ ለመጠቀም እንዲችሉ መደገፍ፣ | ሀ) የተለያዩ የጥናትና ምርምር ዘዴዎችን፣ ንድፈ ሃሳቦችንና የመረጃ አሰባሰብ ቴክኒኮችን መገምገም፣<br>ለ) የመረጃ ስብሰባና ፍተሻን ለመደገፍ አመቺ ቴክኖሎጂንና የቴክኖሎጂ አገልግሎቶችን እንደተገቢነታቸው መጠቀም፣<br>ሐ) ለጥናትና ምርምር ተገቢ የመረጃ ምንጮችንና አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉትን ማግኘት፣<br>መ) የተሰበሰቡ መረጃዎችና ለፍተሻ ተግባር ላይ የዋሉ መሳሪያዎችን ግልጽነት በመጠበቅ የጥናትና ምርምሩን ተገቢነት የተሻለ ማድረግ፣ |
| 2.3 የትምህርት ቤት መምህራንና ርዕሰ መምህራን መረጃን በመመርመር ግኝቶችን ለማቅረብ እንዲችሉ መደገፍ | ሀ) በጥናትና ምርምሮች ለተገቢ አቀራረቦች ፍላጎቶችን መለየት፣<br>ለ) ትምህርታዊ የጥናትና ምርምር ስተራተጂ ተገቢነትን ለማረጋገጥ መረጃ በመሰብሰብ መፈተሽ፣<br>ሐ) ከሕግ አኳያ የጥናትና ምርምሩን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ መረጃንና የጥናትና ምርምሩን ግኝቶች መገምገም፣<br>መ) ከሚመለከታቸው አካላት ፍላጎቶች ጋር በሚሄድ አኳኃን የጥናትና ምርምር ግኝቶችን በግልጽ ማቅረብ፣<br>ሠ) የጥናትና ምርምር ግኝቶች በመማር ስትራቴጂ ላይ እንዴት ተፅዕኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉ መገምገም፣ |

PCSSSE12A2**: በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ20012 የፀደቀ የመጀመሪያ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ 2*

## የሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ 3

| የስታንዳርድ ርዕስ | በትምህርታዊ ተግባራት ክንውኖች ሂደት ወቅታዊ እውቀትንና ግንዛቤን ጥቅም ላይ ማዋል። |
|---|---|
| ስታንዳርድ ኮድ | PCSSSE12A3* |
| ንዑሳን ስታንዳርዶች | የክንውን አመላካቾች |
| 3.1 ትምህርት ቤቶች የመማር ተግባራት ክንውኖችን እንዲያሻሽሉ ለመደገፍ የወቅቱን የትምህርታዊ ተግባራት ክንውኖችን መገምገም፤ | ሀ) የመማር ዘዴዎችን ከወቅታዊ የመማር ስትራቴጂዎች ተገቢነት አኳያ በመመልከት መመዘን፣<br>ለ) ልምድን፣ ግላዊ ምርጫዎችንና የተማሪዎች የመማር ዘዴዎችን መሠረት በማድረግ የተሻሻሉ የመማር ተግባር ክንውንን ማቀድ፣<br>ሐ) የተሻሻሉ አቀራረቦችን በማዘጋጀት ለመሞከር እድገቶችን ወይም ለውጦችንና በመማር ተግባር ክንውን ሂደት ውስጥ ያሉ ተግዳሮቶችን መገምገም፣<br>መ) የተሻሻሉ የመማር ተግበራት ክንውንን ለማበረታታት የተገቢ ግለሰቦችን ምርጫዎች፣ ችሎታዎች፣ ግንኙነቶችና ተጨባጭ ፍላጎቶችን መፈተሽ፣<br>ሠ) የተለያዩ ተገቢ የመማር ንድፈ ሃሳቦችና የመማር- ማስተማር እቅድ ዝግጅት መርሆዎች በትምህርት ቤቶች የመማር ተግባራት ክንውኖችን እንዴት ማሻሻል እንደሚችሉ መገምገም፣ |
| 3.2 ትምህርት ቤቶች የተሻሻሉ የመማር ክንውኖችን በመቀበልና በማስማማት የራሳቸውን አደረጃጀቶችና አሠራሮችን በመቀየስ እንዲተገብሩ ማስቻል፣ | ሀ) የት/ቤት እቅድ ዝግጅትና ትግበራን ለመደገፍ ተገቢ የአመራር ወይም የአስተዳደር መዋቅር እንዲኖር አስተያየት ወይም ሀሳቦችን መስጠት፣<br>ለ) በመማር-ማስተማር ሂደት ለሚሳተፉ ሁሉ ግልፅና ተደራሽ የሆነ የእቅድ ዝግጅት መመሪያና ሥርዓት ተዘጋጅቶ በሰነድነት እንዲያዝ ማድረግ፣<br>ሐ) ት/ቤቶች አጠቃላይ ስትራተጂያዊ ግቦችን በመለየት ግልጽና ሊለኩ ወደሚችሉዝርዝር ዓላማዎች ለመመንዘር እንዲችሉ መደገፍ፣<br>መ) ት/ቤቶች ስትራቴጂክ ተግባራቸውንና ክንውናቸውን በማስተዳደር ማሻሻል እንዲችሉ መደገፍ፣<br>ሠ) የት/ቤት ርዕሰ መምህራን የአመራርና የአስተዳደር ጽንሰ ሃሳቦችን በመጠቀም የት/ቤት መሻሻል ፕሮግራምን በማዘጋጀት እንዲመሩና እንዲያስተዳድሩ ማበረታታት፣<br>ረ) ት/ቤቶች በእቅድ ዝግጅትና ትግበራ ሂደቶችና ሪፖርቶች አቀራረብ ተገቢ ስተራቴጂክ አጋሮችን በመለየትና በመደራደር ተሳትፎአቸውን ማስጠበቅ እንዲችሉ መደገፍ፣<br>ሰ) ት/ቤቶች የተማሪዎች ውጤቶችን ከፍ ለማድረግ የት/ቤት እቅድና ትግበራ ከተማሪዎች ፍላጎቶች ጋር መጣጣሙን ለማረጋገጥ እንዲችሉ በመምከር ማገዝ፣<br>ሸ) ት/ቤቶች የት/ቤቶች ውጤቶችን፣ ዝንበዛሌዎችንና ርዕሰ ጉዳዮችን ከተገቢ ባለድርሻ አካላት ተወካዮች ጋር ተገቢ የግምገማ እቅድን በማዘጋጀት መመርመር እንዲችሉ መደገፍ፣<br>ቀ) ት/ቤቱ በሚጠይቀው መሠረት አስፈላጊውን ግምገማ በማጠናቀቅ የሚፈለጉ ሪፖርቶችን ሁሉ ለተገቢ ባላድርዎች በማቅረብ ግብረመልስ መስጠት፣ |
| 3.3 ውጤታማ የትምህርት ቤት አገልግሎቶችን በማበረታታት መምራት፣ | ሀ) የባለድርሻዎችን ድጋፍ ለማበረታታት የተለያዩ የተግባቦት መሣሪያዎችንና ተግባራትን በመጠቀም ስለት/ቤቱ ተግባራትና ውጤቶች መረጃዎችን ማሠራጨት፣<br>ለ) የት/በቶቹን አገልግሎቶች ለማስተዋወቅ እድሎችን በመፈለግ በሚገኘው ሚዲያ ሁሉ መጠቀም፣<br>ሐ) የት/ቤት ተግባራትንና ውጤቶችን ለማስተዋወቅ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ |

| | |
|---|---|
| | መረቦችን መጠቀም፣<br>መ) ለውጤታማና ስኬታማ የተግባራትና የአገልግሎቶች ቅንጅት ዘዴዎችን በመለየት መተግበር፣<br>ሠ) በተገለጹ አሠራሮች ትግበራ ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችን ለማስወገድ መሥራት፣<br>ረ) የት/ቤት ተግባራትንና ውጤቶችን በትክክል የሚገልጹ ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ለተገቢ ባለድርሻዎችና አስተዳደሮች ማቅረብ፣<br>ሰ) ውጤታማ፣ በመረጃ ላይ የተመሠረቱ ውይይቶችንና ውሳኔን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የአስተዳደር ቦርድ ስብሰባዎችን ማገልገል፣ |
| 3.4 ለትምህርት ቤቶች መሻሻል ተገቢ ግብረ መልሶችንና ድጋፎችን ለመስጠት የክትትልና ግምገማ ፕሮግራምን በማቀድ ማዘጋጀት፣ | ሀ) የግምገማ ዓለማዎችንና መጠንን በማዘጋጀት በሰነድነት መያዝ፣<br>ለ) የሚፈለገውን መረጃ በመለየት ምንጩን ማግኘት፣<br>ሐ) ተግባራትንና በግምገማው ተሳታፊ ባለድርሻዎችን የለየ የፕሮጀክት እቅድና የጊዜዜ ሳሌዳን መፍጠር፣<br>መ) በግምገማው የሚሳተፉ ሠራተኞችን በመምረጥ አጭር መግለጫ መስጠት፣<br>ሠ) በግምገማው እቅድ ዝግጅት ላይ ከተሳተፉ የባለድርሻ አካላት ጋር ገንቢ ግንኙነት መፍጠር፣<br>ረ) በተግባራት ክንውን ላይ ተፅዕኖ ያሳደሩ ሁኔታዎችን በመለየት የመማር-ማስተማንሩ ሂደት ማሻሻል በሚቻልባቸውን አማራጮች ላይ አስተያየቶችን መስጠት፣<br>ሰ) በግምገማው ዓላማና መጠን መሠረት የመማር-ማስተማር ውጤታማነትና ስኬታማነትን በማስመልከት ግብረ መልሶችን በማዘጋጀት መስጠት፣ |

PCSSSE12A3*: *በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ20012 የፀደቀ የመጀመሪያ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ 3*

## የሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ 4

| የስታንዳርድ ርዕስ | **ውጤታማና አሳታፊ የትምህርት ቤት አመራርና አስተዳደርን መተግበር** |
|---|---|
| ስታንዳርድ ኮድ | PCSSSE12A4 |
| ንዑሳን ስታንዳርዶች | የክንውን አመላካቾች |
| 4.1 ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደት አመራር ለማረጋገጥ ለመምህራንና ርዕሰ መምህራን ድጋፍ መስጠት፣ | ሀ) በስትራቴጂያዊና በዝርዝር ሥራ እቅዶች ዝግጅት ላይ መምህራንንና ርዕሰ መምህራንን መደገፍ፣<br>ለ) በውጤታማ የማስተማሪያ ክፍሎች አያያዝና አስተዳደር ላይ መምህራንን መደገፍ፣<br>ሐ) መምህራን ስኬታማ፣ ወጤታማና አሳታፊ የማስተማር ዘዴዎችን በመለየት መተግበር እንዲችሉ መደገፍ፣<br>መ) ስኬታማ፣ ውጤታማና ግልፅ የምዘና ዘዴዎችን በማስመልከት ሃሳቦችን በመስጠት መምህራንን መደገፍ፣ |
| 4.2 ውጤታማና አሳታፊ የትምህርት ቤት አስዳደርን ማረጋገጥ | ሀ) በመምህራንና በአስተዳደር ሠራተኞች መካከል ጠንካራ ትስስርን መፍጠር፣<br>ለ) ት/ቤቶች ስኬታማና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ የትምህርት ቤት ሪሶርስ አያያዝና አስተዳደር መተግበር እንዲችሉ መደገፍ፣<br>ሐ) ት/ቤቶች በ/ቤቶች አመራርና አስተዳደር የማበረሰቡን ተሳትፎ ለማረጋገጥ እንዲችሉ ማበረታታት፣<br>መ) ት/ቤቶች ሁልጊዜ የተግበራት ክንውኖቻቸውን በመከታተል እንዲገመግሙ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት፣ |

| | |
|---|---|
| 4.3 በለውጥ አስተዳደርና አያያዝ የስትራቴጂያዊ ለውጥ አስፈላጊነትና ለለውጡ ያሉ እድሎችን በሚመለከት ሃሳቦችን ወይም አስተያየቶችን መስጠት | *ሀ) ስትራቴጂያዊ የለውጥ ፍላጎቶችን ለመለየት ከስትራቴጂያዊ ዓላማዎች አንጻር ያሉ የት/ቤት ተግባራት ክንውኖችን መገምገም፣*<br>ለ) ከውጫዊ አካባቢ በትምህርት ዓላማዎችና ስኬቶች ወይም ውጤቶች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ አሠራሮችንና እንቅስቃሴዎችን ለመለየት ክትትል ማድረግ፣<br>ሐ) ከተግባራዊ ክንውን ክፍተቶች፣ እድሎች ወይም ፈታኝ ሁኔታዎች ወይም የአስተዳደር ውሳኔዎች የተነሳ ለውጥ የሚያስፈልጉ አሠራሮችን መለየት፣<br>መ) በስኬታማ ተግባቦት ለውጥ በመለየት ሂደት ባለድርሻዎችን ማሳተፍ፣<br>ሠ) ቁልፍ የለውጥ ፍላጎቶችንና እድሎችን በመለየት ሂደት ባለሙያዎችን በማማከር እገዛ ማግኘት፣<br>ረ) ከተገቢ አስተዳዳሪዎች ጋር ለውጥ የሚያስፈልጉትን ወይም የለውጥ እድሎችን በመገምገም ቅደም ተከተል ማስያዝ፣<br>ሰ) ቅድሚያ ለተሰጠው የለውጥ ፍላጎቶች ወይም እድሎች የወጪና የጥቅም ፍተሻና ምርመራ ማድረግ፣<br>ሸ) ለፈታኝ ሁኔታዎች ፍተሻና ምርመራ በማድረግ፣ የለውጥ መሰናክሎችን በመለየት፣ ለመፍትሔ ስትራተጂዎችን በመንደፍና በመስማማት መዝግቦ መያዝ፣<br>ቀ) የለውጥ አያያዝና አስተዳደር ስትራቴጂ ትግበራን በመከታተል መገምገም፣ |
| 4.4 ተገቢ የተማሪዎች ልዩነቶች አስተዳደርና አያያዝ ሥርዓት እንዲኖራቸው ለትምህርት ቤቶች ድጋፍ መስጠት | ሀ) የተገቢውን ፖሊሲ ትግበራ ለመደገፍ በትምህርት ቤት የተማሪዎች የልዩነቶች አያያዝና አስተዳደር ልምዶችን መፈተሽ፣<br>ለ) በትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ልዩነቶች አያያዝን በተመለከተ የጋራ ግንዛቤ ለመፍጠር ከተለያዩ እይታዎች አንጻር ቁልፍ የልዩነት ነጥቦችን በመለየት መግለጽ፣<br>ሐ)ትምህርት ቤቶች በተማሪዎች ልዩነቶች አያያዝና አስተዳደር ልቀው እንዲገኙ የተማሪዎች ልዩነቶች አያያዝ ንድፈ ሃሳባዊና የተሞክሮ ሞዴሎችን በመገምገም መደገፍ፣<br>መ) ትምህርት ቤቶችን በተገቢ የተማሪዎች ልዩነቶች አያያዝና አስተዳደር ስትራቴጂ ዝግጅትና ትግበራ መደገፍ፣<br>ሠ) በትምህርት ቤቶች ለተሻሻሉ የተማሪዎች ልዩነቶች አያያዝና አስተዳደር ስትራቴጂዎችና ክንውኖች ግብረ መልሶችን ለመስጠት የስትራቴጂዎቹን ትግበራ በመከታተል መገምገም፣ |
| 4.5 መሻሻልን፣ ፈጠራንና ለውጥን መምራት | ሀ) ለፈጠራ አስተሳሰብ መዳበር ለሥርዓቱ ጽንሰ ሃሳቦችንና አማራጮችን ማመንጨት፣<br>ለ) ፈጠራንና መሻሻልን የሚደግፍ አካላዊ አካባቢን ለመፍጠር ከትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራንና ማህበረሰብ ጋር መሥራት፣<br>ሐ) መሻሻሎችንና የፈጠራ ተግባራት ክንውኖችን መምራት፣<br>መ) የፈጠራ ባህልን በመፍጠር እንዲዳብር መደገፍ፣<br>ሠ) ለፈጠራ አስተሳሰቦችና ተግባራት ክንውኖች አስተማማኝነትን ለመደገፍ ስትራቴጂዎችን በማዘጋጀት መተግበር፣ |

PCSSSE12A4*: *በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ20012 የፀደቀ የመጀመሪያ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ 4*

## የሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ 5

| የስታንዳርድ ርዕስ | **በትምህርት ቤቶች ሊሟሉ የሚገቡ አስፈላጊ ሁኔታዎችን መለየትና መተርጎም፣** |
|---|---|
| ስታንዳርድ ኮድ | PCSSSE12A5* |
| ንዑሳን ስታንዳርዶች | የክንውን አመላካቾች |
| 5.1 የትምህርት ቤት ሥራና አሠራር ስፋትን ወይም መጠንን ግልጽ ማድረግ | ሀ) በት/ቤቶች የሥራ መስክ አደረጃጀቶችና እቅዶች የተለያዩ ተገቢ አሠራሮችን በመለየት መገምገም፣<br>ለ) የት/ቤቶች አሠራሮችና የሥራ አደረጃጀት ፍተሻ በማካሄድ የት/ቤት ሥራዎች የሆኑትን መለየት፣<br>ሐ) እቅዶችን በተገቢ የድርጅት ሃላፊ በማፀደቅ ለት/ቤቶች መግለጽ፣<br>መ) በት/ቤቶች ሊሟሉ ከሚገቡ አስፈላጊ ሁኔታዎች ጋር በተዛመደ ሁኔታ ት/ቤቶች ስለሥራቸውና አሠራራቸው ስፋት ያላቸውን ግንዛቤ በመከታተልና በመደገፍ መገምገም፣ |
| 5.2 ትምህርት ቤቶች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ሁኔታዎችን መለየት፣ | ሀ) ተገቢ ምንጮችን በመጠቀም ሊሟሉ የሚገቡ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎችን በሚመለከት መረጃዎችን የማፈላለግ ሥራዎችን ማካሄድ፣<br>ለ) ከሁሉም ተገቢ ሕጎች፣ ደንቦች፣ ድርጅታዊ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች አኳያ በመፈተሽ ሊሟሉ የሚገቡ ተገቢ ሁኔታዎችን መለየት፣<br>ሐ) የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለ/ቤቶች አሠራርና አገልግሎት ባላቸው ተገቢነት መሠረት በየጊዜው በመገምገም ማሻሻል፣<br>መ) ሊሟሉ በሚገቡ ተገቢ ሁኔታዎች ዙሪያ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለቀጣይ ፍተሻ በተገቢው ፎርማት በመደራጀት ማስቀመጥ፣ |
| 5.3 የተለዩ ትምህርት ቤቶች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ሁኔታዎችን መተርጎም፣ መፈተሽና ቅደም ተከተል ማስያዝ | ሀ) የተሰበሰቡ መረጃዎችን በትምህርት ቤቱ ሥራዎች፣ አገልግሎቶችና ውጤቶች መሠረት መገምገምና መተርጎም፣<br>ለ) ሊሟሉ የሚገቡ ሁኔታዎቸን በሚመለከት ተለይተው የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመተርጎሙ ሂደተ ግልጽ ባልሆኑና ባጋጠሙ ችግሮች ላይ ተገቢ ከሆኑ ወጫዊና ውስጣዊ የሥራ ኃይሎች ጋር መወያየት፣<br>ሐ) ሊሟሉ የሚገቡ ሁኔታዎችን ለት/ቤቶች ካላቸው እንድምታና ጥሰታቸው ሊያስከትል ከሚችለው ፈታኝ ሁኔታዎች አንጻር መለየት፣ መፈተሽና ቅደም ተከተል ማስያዝ፣<br>መ) ሊሟሉ የሚገቡ ሁኔታዎችን እንደሚከተለው መክፈል፦<br>• ለት/ቤቶች አሠራር ቁልፍና ወና ወይም ማዕከል የሆኑ፣<br>• በተወሰኑ ሁኔታዎች ጠቃሚ የሆኑ፣ ነገር ግን ለት/ቤቶች አሠራር ማዕከል ያልሆኑና<br>• ተገቢ የሆኑ፣ ነገር ግን ለት/ቤቶች አሠራር የላቸው አስተዋጽኦ አናሳ የሆነ፣ |
